የሰ.መ. ቁ. 23667

7/10/98

ዳኞች 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

2. ›› ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. ›› ጌታቸው ምህረቱ

4. ›› መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢት/የእህል ንግድ ድርጅት

ተጠሪ ፡- አቶ ግርማ ተገኝ

## ፍርድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14919 በ04/02/98 የተሠጠው ውሣኔ ነው፡፡

ተጠሪ ያላግባብ ከሥራ ስለተሠናበቱ ወደ ሥራ የመመለስ ክስ መስርተው ፍ/ቤቱ በ14/11/96 ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ ነገር ግን አመልካች ወደ ስራቸው የመለሣቸው በ07/4/97 በመሆኑ ውሣኔ ከተሠጠበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሥራ እስከተመለሱበት ጊዜ ያለው ደሞዝ እንዲከፈላቸው በ11/9/97 በተፃፈ የክስ አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ወደ ስራ እንዲመለሱ ከተወሠነበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ያለው ከ10 ወር በላይ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል በማለት ተቃውሟል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ይርጋው ጊዜ መቆጠር መጀመር ያለበት ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ሣይሆን ወደ ስራ ከተመለሱበት ጊዜ ጀምሮ ነው በማለት የይርጋውን ጥያቄ ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪ የ4 ወራት ደሞዝ እንዲከፍል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ይህ ችሎትም የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠርን በተመለከተ ለመመርመር አቤቱታውን ለሠበር አስቀርቦ ተጠሪም ቀርበው ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ______ ቀን 11-11-98

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የተወሰነው በ14/11/96 ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወደ ሥራቸው በመመለስ ደመወዝ የማግኘት መብታቸውን ያገኙት ይኸው ውሣኔ ከተሰጠበት ዕለት ጀምሮ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን መብታቸውን ለመጠቀም የሚችሉት መቼ ነው የሚለውን ስንመለከት በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 163(1) ሥር በአዋጁ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በቀር የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ደመወዝ ለመጠየቅ የሚችሉት ወደ ስራ እንዲመለሱ ውሳኔ በተሠጠበት ወር ውስጥ የመ/ቤቱ የደመወዝ መክፈያ ከሚውልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደመወዝ እንዲከፈላቸው ስለሆነ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄያቸውን ሊያቀርቡ የሚገባው የወሩ ደመወዝ ከሚከፈልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ ለመሆኑ ከአዋጁ አንቀፅ 162(3) እንመለከታለን፡፡ ተጠሪ የጠየቁት ወደ ስራ እንዲመለሱ ከተወሠነበት ቀን ጀምሮ ስራ እስኪጀምሩበት ጊዜ ያለውን የ4 ወራት ደመወዝ ሲሆን ክስ የመሠረቱትም በ11/09/97 ነው፡፡ ከነዚህ የ4 ወራት ደመወዝ ውስጥ የየወሩ ደመወዝ መጠየቅ ከሚቻልበት ቀን ጀምሮ (የደመወዝ መክፈያ ቀን) ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ያለውና የ6 ወር ጊዜ ያላለፈበት ደግሞ የህዳር ወር ደመወዝ ብቻ ነው፡፡

በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከውሣኔው ቀን ጀምሮ ሣይሆን ተጠሪ ወደ ስራ ገበታቸው ከተመለሱበት ቀን ጀምሮ ነው በማለት የ4 ወራት ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሠናቸው ስህተት ነው፡፡

## ውሣኔ

1) የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14919 በ04/02/98 የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 42747 በ18/04/98 የሠጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2) አመልካች ለተጠሪ የህዳር ወር ደመወዛቸው ብቻ ይከፈላቸው፡፡
3) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ...
ቀን 11-11-98